የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 44
ADDIS ABABA 30th April 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፪/፪ሺ፯ ዓ.ም

በተደጋጋሚ የተከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ የሚያስችለውን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ…………ገጽ ፰ሺ፪፻፵፫

CONTENTS

Proclamation No. 892/2015

Government of the Italian Republic Loan Agreement for financing Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Programme Ratification Proclamation………….Page 8243

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፪/፪ሺ፯ ዓ.ም

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

በተደጋጋሚ የተከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ የሚያስችለውን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፲፪ ሚሊዮን ዩሮ (አስራ ሁለት ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ጥር ፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚ ከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 892/2015

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFAY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE ITALIAN REPUBLIC</u>**

WHERE AS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic provide to the Government of the Federal Democratic republic of Ethiopia a Loan amount of 12,000,000 Euro (Twelve Million Euro) for financing Drought Resilience and Sustainable Livelihood Programme was signed in Addis Ababa on the 15th day of January 2015;

WHEREAS, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Re[public of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 31st day of March 2015;

NOW THEREFORE; in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia ,it is here by proclaimed as follows:

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በተደጋጋሚ የተከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ የሚያስችለውን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል የብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፪/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as the" Government of the Italian Republic Loan Agreement for financing Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Programme Ratification Proclamation No.892/2015."

**፪.የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ጥር ፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed in Addis Ababa on the 15th day of January 2015 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፪ ሚሊዮን ዩሮ (አስራ ሁለት ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**3. Power of Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 12,000,000 Euro (Twelve Million Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

Done at Addis Ababa, this 30th day of April, 2015.

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት